# በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
# Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*መጋቢት 12 ቀን 2006ዓ.ም*

*ለአገር ወደድ ኢትዮጵያውያን በያሉበት*

*በሰደት ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ የቀረበ የድጋፍና የርዳታ ጥሪ*

*ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሲቪል ማህበራት አመርቂ ተሳትፎ በሁሉም መስክ ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ይታመናል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ለአገሪቱ ያበረከተው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በጎ አስተዋጽኦ ቀላል የማይባል ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ማህበሩ የመምህራንን ሙያ ክብርና ጥቅም ለማስጠበቅ ፣ የትምህርቱን ጥራትና በእኩልነት መዳረስን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የመልካም አስተዳደርና ፍትህ መስፈንን እውን ለማድረግ፣ ባጠቃላይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ ለማገዝ በነፃነት መደራጀትን ቅድሚያ ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ አመራሩም ሆነ አባላቱ ዘርፈ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል።እየከፈሉም ነው። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ መምህራን መሪ ድርጅታቸው በአምባገነኑ የወያኔ ሥርዓት ፈርሷል፤ ጽ/ቤታቸውን ፣ ንብረታቸውን ፣ ገንዘባቸውንና መብታቸውን ተነጥቀዋል።ይህን አስካፊ የመብት ረገጣ ለማስወገድ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ የበኩሉን ለመወጣት ተቋቁሟል። ኮሚቴው ከተቋቋመበት ከታሕሣሥ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ፡-*

- *በተለያየ ምክንያት ከአገራቸው የወጡ መምህራንንና ደጋፊዎችን ለመድረስና ለማሰባሰብ ጥረት አድርጓል በማድረግም ላይ ይገኛል፣*
- *አገር ቤት ውስጥ ካሉት መምህራን ጋር ግንኙነት ለማድረግና ለማደራጀት ወስኖ አቅም በፈቃደ መሰረት ሥራዎችን እያከናወነ ነው፤ጥሩ ውጤትም ተገኝቷል።*
- *በመምህራን ላይ፣ በትምህርቱ ዘርፍና አብረውን ሊቆሙ በሚችሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ በሥልጣን የሚገኘው የወያኔ መንግሥት የሚፈጽመውን ወንጀል መምህራንና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቁና በትግሉም እንዲሳተፉ የተለያዩ መግለጫዎችን አውጥቷል።*

*ይበልጥ መምህራንን ለማድረስና ለማደራጀት የአገር ወደድ ኢትዮጵያውያን ድጋፍና ርዳታ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም በሚከተለው የባንክ አድራሻ ርዳታዎን እንዲያደርጉልን ኮሚቴው ከከበረ ሰላምታ ጋር ጥሪ ያቀርባል። አስተያየትዎንም ታች በሚገኙት የግንኙነት መስመሮች እንዲልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን።*

*Direct to : Wells Fargo Bank , N.A, 420 Montgomery Street, San Francisco, CA 94104*

*Routing Number : 121000248 Account number : 6852542643*

*Account legal Name : CCEMETA*

*Swift code : (used for international wires only) WFBIUS6S*

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com